# ልጅዎን ከ COVID-19 ይጠብቁ

### ፅሁፍ

[አነቃቂ መዚቃ]

[ትረካ]

የ COVID-19 ክትባት ዕድሜያቸው 6 ወር እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልጆች በአሁኑ ሰዓት ይገኛል።

የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል ዕድሜያቸው 6 ወር እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሁሉም ልጆች እንዲከተቡ ይመክራል።

የ COVID-19 ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ነጻ እና ለልጆች ውጤታማ ነው። ክትባቶቹ ጥናት ተደርጎባቸው ለሁሉም ልጆች እና ታዳጊዎች እንድሰጥ ከመመከራቸው በፊት ደህንነታቸው የተጠበቀ እንደሆነ ታይቷል።

እንደ አዋቂዎች፣ በሁሉም ዕድሜ ያሉ ልጆች እና ታዳጊዎች በ COVID-19 በጣም ሊታመሙ ይችላሉ፣ የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ የጤና ችግሮች ሊኖራቸው ይችላል፣ እንዲሁም COVID-19 ን ወደ ሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

ልጆች እና ታዳጊዎች በ COVID-19 እንዴት ሊጎዱ እንደሚችሉ አስቀድሞ ለመናገር ምንም አይነት መንገድ የለም። ስር የሰደዱ የህክምና ሁኔታዎች ያሉባቸው ወይም ደካማ በሽታ የመከላከል ስርዓት ያላቸው ሰዎች በ COVID-19 በጣም የመታመም ከፍተኛ ዕድል አላቸው። ነገር ግን ጤናማ የሆኑ ልጆችም እንኳን በጠና ታመዋል። ክትባት በጣም አስፈላጊ የሆነውም ለዚህ ነው።

በ COVID-19 ተይዘው የነበሩ ልጆችም እንኳን መከተብ አለባቸው ምክንያቱም ተጨማሪ ጥበቃ ይሰጣል። ከአንዴ ጊዜ በላይ በ COVID-19 የመያዝ ዕድል አለ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት የሆነ ሰው መለስተኛ በሽታ ነበረው ማለት እንደገና እንደዚያ ይሆናል ማለት አይደለም።

የ COVID-19 ክትባት የ COVID-19 ህመምን አያስከትልም። የክንድ ቁስለት ወይም አነስተኛ ትኩሳት የመሳሰሉ የተወሰኑ የጎንዮሽ ጉዳቶች ከክትባት በኋላ የተለመዱ ናቸው እንዲሁም ከአንድ ወይም ሁለት ቀናት በኋላ ይጠፋሉ።

የ COVID-19 ክትባት ቤተሰቦችን እንዲሁም ማህበረሰቦችን ከ COVID-19 ለመጠበቅ ይረዳል።

ጥሩ ጥበቃ ለማግኘት ለልጅዎ የሚመከሩ የ COVID-19 ክትባት ሁሉም ዶዞች ያስፈልጉታል – ይህም አጋዥ ዶዝችን ሊያካትት ይችላል።

ለህጻናት ልጆች የሚሰጡ ክትባቶች ለትልቅ ልጆች ወይም አዋቂዎች ከሚሰጡት ክትባቶች አነስ ያለ ዶዝ ነው። የክትባቱ ዶዝ መጠን በልጆቹ ዕድሜ ላይ መሰረት ያደረገ ነው፣ በመጠናቸው ወይም በክብደታቸው አይደለም።

ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ካለው/ካለቸዉ፣ ተጨማሪ መረጃ መስጠት ይችላሉ እንዲሁም የመጀመሪያ ዶዝ በሚያገኙበት ጊዜ ሁሉንም የሚመከሩ ዶዞች መርሃ ግብር እንዲይዙ ይረዳዎታል። ልጆች የ COVID-19 ክትባትን እንዲሁም ሌሎች የሚያስፈልጓቸውን ክትባቶች በተመሳሳይ ጉብኝት ማግኘት ይችላሉ።

ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌለው፣ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እንዲሁም በአቅራቢያዎ ያሉ የክትባት ጣቢያዎችን ለመፈለግ mn.gov/vaxforkids ን ይጎብኙ። የሚኒሶታ የጤና መምሪያ የ COVID-19 የስልክ መስመር ጥያቄዎችን ለመመለስ በስራ ላይ ይገኛል፣ እንዲሁም እርስዎን በተለያዩ ቋንቋዎች ለማናገር ይገኛሉ። በ 1-833-431-2053 ነጻ መስመር ይደውሉ።

የዝቅተኛ-ዋጋ የጤና እንክብካቤ ወይም የጤና መድህን ለማግኘት የሚረዱ የመረጃ ምንጮች (www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/materials/lowcost.html) በተለያዩ ቋንቋዎች ለማግኘት የሚኒሶታ የጤና መምሪያ ድረገጽን ይጎብኙ።

[ጥዑም መዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975
health.communications@state.mn.us

10/19/2022 (Amharic)
ይህን መረጃ በተለየ ቅርፀት ለማግኘት፣ በሚከተለው ይደውሉ፦ 651-201-4989